# ስምንተኛ ትምህርት ከየካቲት 11 — 17 Feb 18—24

## መንፈስ ቅዱስና የመንፈስ ስጦታዎች

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 12:4-7፣ 11፣ ኤፌ. 4:7፣ 1ቆሮ. 12:14-31፣ ሮሜ 12:3-8፣ 1ዮሐ. 4:1-3.

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፦ "ስጦታዎች ልዩ ልዩ ሲሆኑ ፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራሩም ልዩ ልዩ ሲሆን ፤ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው።" (1 ቆሮ. 12:4-6)**

አባት ለሥራ ራቅ ወዳለ ስፍራ ሊጓዙ በመሆኑ እርሳቸው እስኪመለሱ ልጃቸው ቤቱን እንዲያስተዳድር ኃላፊነት ይሰጡታል። ነገር ግን ልጅ የተሰጠውን ኃላፊነት በትክክል ለመወጣት የሚያስችለው ገንዘብም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች ሳይሟሉ መቅረታቸውን ብዙም ሳይቆይ ይረዳል። እቅዱን መተግበር ያልቻለው ልጅ በሁኔታው ያዝንና የተባለውን ሳይሠራ ይቀራል።

በተመሳሳይ የሱስ ደቀ መዛሙርቱን ትቶ ከአባቱ ጋር ለመሆን ወደ ሰማይ ሲሄድ በተለይ የሚሠሩትን ሥራ ሰጥቶአቸው ነበር--ወንጌልን ለዓለም እንዲሰብኩ። ነገር ግን የሱስ መልእክቱን ለማስራጨት አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ ሳያሟላላቸው እንደው በባዶ ትቶአቸው አልሄደም። በስሙ እንዲሠሩ ያዘዛቸውን ወደ ተግባር እንዲለውጡ ያስቻላቸው ሲሆን ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና እገዛ ነበር። ጳውሎስ በ1ቆሮ. 1፡ 4-7 የሚከተለውን ምስጋና ያቀርባል፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ተሰጣችሁ ጸጋ ዘወትር ስለናንተ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ… ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታ አይጎድልባችሁም።" ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ--በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መንፈሳዊ ስጦታዎች ይሰጣሉ።

በዚህ ሳምንት መንፈስ ቅዱስ አስገራሚውን የእግዚአብሔር ስጦታ የሚሰጠን ብቸኛው ኃይል መሆኑን እንዲሁም በመንፈስ ፍሬና በመንፈስ ስጦታዎች መካከል ያለውን ልዩነት እናጠናለን።

*እሑድ የካቲት 12* *Feb 19*

### የመንፈስ ፍሬና የመንፈስ ስጦታዎች

የመንፈስ ፍሬና የመንፈስ ስጦታዎች--ሁለቱም የሚሰጡት ከአንዱ መንፈስ ቅዱስ ነው። ነገር ግን ተመሳሳይ አይደሉም። ማንም የመንፈስን ስጦታ እንዲያንጸባርቅ ባይጠየቅም--ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የመንፈስን ፍሬ ሊያሳይ ይገባል። የመንፈስ ስጦታዎች የአንድን ሰው ጥልቅ መንፈሳዊነት ያን ያህል ባያሳዩም የመንፈስ ፍሬዎች ግን ያሳያሉ። አንድ ብቻ ፍሬ ያለ ሲሆን ስጦታዎች ግን ብዙ ናቸው። አንዳንድ ስጦታዎች ከሌሎች የመብለጥ ባህሪ አላቸው።

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--1ቆሮ. 12፡4-7፣ 11 የጳውሎስ አስተምህሮ አበይት ፍሬ ነገር ምንድን ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እግዚአብሔር በተከታዮቹ ሕይወት እንዲታዩ በማቀድ ፈርጀ ብዙዎቹን የመንፈስ ፍሬዎች የቀመረ ሲሆን፤ ነገር ግን እያንዳንዱ አማኝ ከሌላው ጋር ተመሳሳይ ስጦታ ወይም ስጦታዎች አልተሰጠውም፡፡ ሁሉም ሰው በተለይ አንድ ዓይነት ስጦታ ይኑረው የሚል ትእዛዝ የለም--ለምሳሌ በልሳን እንደ መናገር ያሉ፡፡ በዚህ ፋንታ ኃያሉ አምላክ ገጣሚ ያለውን ስጦታ ለአማኞች ይሰጣል፡፡ የመንፈስ ስጦታዎች የሚሰጡን ሌሎችን እንድናገለግልና የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያኑን እንድናንጽ ነው፡፡ በመሆኑም ስጦታዎቹ የሚሰጡን ለራሳችን ደስታና ክብር ሳይሆን ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሥራ ወደፊት እንድናራምድ ነው፡፡

ስለዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች የመንፈስ ፍሬ ከሌላቸው በቀር ዋጋ ቢሶች ናቸው፡፡ ፍቅር--ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ዐውድ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ ማየታችን አስደናቂም፣ አስደሳችም ነው፡፡ ከ 1ቆሮ. ምዕ. 12 ቀጥሎ የሚመጣው ምዕራፍ--ከፍ ባለ ማዕረግ የተጠቀሰው ፍቅር ነው፡፡ እንዲሁም ከኤፌ. 4፡11-13 በቀጣይነት የሚመጡት ቁጥሮች--ማለትም 15 እና 16 ስለ ፍቅር ማጣቀሻዎች ይሰጡናል፡፡ በተመሳሳይ የመንፈስ ስጦታዎች ከተጠቀሱበት--ሮሜ 12፡3-8 በመቀጠል የቀረቡት ቁጥሮች ሰለ ፍቅር ይናገራሉ (ሮሜ 12፡9-10)፡፡

ስጦታዎች እንደ ጸጋ ስጦታነታቸው ያው የፍቅር ስጦታዎች ናቸው፡፡ የተሰጡት ከፍቅር የተነሳ እንደመሆኑ ወደ ሌሎች ሰዎች በመድረስ የፍቅር አምላክ የሆነውን እግዚአብሔር ያገለግላሉ፡፡ ሌሎችን በመውደድ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለእነርሱ እንገልጣለን፡፡ አፍቃሪውና ሁሉን የሚያውቀው አምላክ ሕዝቡ የተሰጠውን ተልዕኮ ከግብ እንዲያደርስ ያዘዘውን ለመፈጸም የሚያስችለውን ማንኛውንም ነገር ያሟላል፡፡ ፍቅር ከሁሉም የላቀ ስጦታ የሆነበት ምክንያት ይኸው ሊሆን ይችላል (1ቆሮ. 13፡13)፡፡

እንደ ክርስቲያንነታችን ፍቅር የምናደርገው የማንኛውም ነገር ማዕከል የሆነው ለምንድን ነው? ፍቅር ለምስክርነታችን "ኃይል" መሆን የሚችለው እንዴት ነው?

*ሰኞ የካቲት 13* *Feb 20*

## የመንፈሳዊ ስጦታዎች ሰጭ የሆነው ሉዐላዊ አምላክ

ምን ዓይነት ስጦታ ሊኖረን እንደሚገባ የምንወስነው እኛው ራሳችን አይደለንም፡፡ ካሪዝማታ የግሪክ ቃል ሲሆን የመንፈስ ስጦታዎች የሚል ፍቺ አለው፡፡ ቃሉ በራሱ በእግዚአብሔር ተከፋፍለው የተሰጡትን የጸጋ ስጦታዎች ያመላክታል፡፡ እነዚህን የጸጋ ስጦታዎች በሰብዓዊ ክብራችን፣ ደረጃችን፣ ትምህርታችን ወይም መንፈሳዊ ብቃታችን ልናገኛቸው አንችልም፡፡ ስጦታዎቹ እግዚአብሔር ያዘዘንን እንድንፈጽም ከፍቅር የተነሳ በነጻ የተሰጡን ናቸው፡፡

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡--ኤፌ. 4፡7፡፡ ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እናስባለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በተመሳሳይ የሱስን ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ሰጪነት ጋር አያይዞ ያቀርበዋል፡፡ የሱስ ስጦታዎችን ከመስጠት ጋር የተያያዘው እንዴት ነው?

ስጦታዎችን ለእኛ ለመስጠት የክርስቶስ ጸጋ ባለ መብት መሆኑን ጳውሎስ ይናገራል፡፡ ነገር ግን ስጦታዎቹን ለቤተ ክርስቲያን አባላት የሚደለድለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ የሱስ ክርስቶስን እንደ ግል

አዳኛቸው አድርገው በእርሱ ለሚያምኑ መንፈስ ቅዱስ "እንደ ፈቀደ" (1ቆሮ. 12:11) መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣቸዋል። ስጦታዎችን መስጠት የእግዚአብሔር ሉዐላዊ ውሳኔ ነው።

የተፈጥሮ ችሎታ የመንፈስ ስጦታ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። መንፈሳዊ ስጦታዎች አንድ ሰው በትምህርት ሊያዳብራቸው ከሚችላቸው የተፈጥሮ ችሎታዎች ጋር ተመሳሳይ አይደሉም። ብዙዎች ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በእነዚህ የተፈጥሮ ችሎታዎች ተባርከዋል። ነገር ግን እያንዳንዱ መልካምና ፍጹም ስጦታ ከእግዚአብሔር እንደ መሆኑ (ያዕ. 1:17) እግዚአብሔር የሌሎችን ክርስቲያኖች ህይወት ለመባረክና ቤተ ክርስቲያኑን ለማሳደግ አማኞቹን በተለያዩ ስጦታዎች መባረክ ውሳኔው ነው። እንዲሁም አንድ ሰው ውሎ አድሮ የችሎታው ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ሲገነዘብ፣ በጸሎትና ራሱን ለእግዚአብሔር በመስጠት ይህን የተፈጥሮ ችሎታውን በጌታ ሥራ ላይ ለማዋል ሲወስን እግዚአብሔር ተፈጥሮአዊውንም ችሎታ መጠቀም ይችላል።

ጳውሎስ በ1ቆሮ. 12:14-31 ስለ መንፈስ ስጦታዎች ድልድል ለአንባቢዎቹ ምን ይላል? መንፈሳዊ ስጦታዎች እንዴት በቤተ ክርስቲያን እንደሚሠሩ አስመልክቶ እንዲህ ያለው አመለካከት በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ስጦታዎችን እንደ ችሎታውና እንደ ፈቃዱ የሚደለድል መንፈስ ቅዱስ ነው። እርሱ የሚወደንና እንዴት በበለጠ እንደምናገለግለው የሚያውቅ እንደ መሆኑ ሌሎች በተሰጧቸው ስጦታዎች ልንመቀኝ አይገባም። በሌሎች ስጦታዎች ላይ የምቀኝነት መንፈስ ማሳየት ለእግዚአብሔር በጎነት ምስጋና ቢስ መሆንና ለእያንዳንዱ እንደ ፈቃዱ የሚደለድለውን አምላካዊ ችሎታ መጠራጠር ነው።

**እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያንዎ አባላት ምን ዓይነት ስጦታዎች ሰጥቶአል? የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ስጦታ አላቸው ከሚለው እውነታ ምን ዓይነት መልእክት መውሰድ ይችላሉ?**

*ማክሰኞ　　የካቲት 14*　　　　　　　　　　*Feb 21*

## የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡-- ሮሜ 12:3-8፣ ኤፌ. 4:8-12። እግዚአብሔር የሚሰጠን መንፈሳዊ ስጦታዎች ዓላማ ምንድን ነው?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በግልጽ እንደ ሚስተዋለው መንፈሳዊ ስጦታዎች ለአገልግሎት እንጂ ራሳችንን እንድንቀድስባቸው አልተሰጡንም። ለማወቅ ጉጉታችን ታምራዊ እርካታ አያጎናጽፉም ወይም የድብርት ስሜት ማርከሻ አይደሉም። ብዙውን ጊዜ አስፈላጊ ስለምንላቸው መንፈሳዊ ነገሮች ማሟላት ስናስብ በአእምሮአችን የሚመጣው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወይም በኃይል የተሞላ መንፈሳዊ ህይወት ነው። የዚህ ውጤት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ክርስቶስን ሳይሆን ክርስትናን ማዕከል ያደረገ አድርጎ ወደ መመልከት ይወስደናል። ይህም ትኩረታችን በእግዚአብሔር ላይ ሳይሆን አብልጦ በራሳችን ላይ እንዲሆን ያደርጋል። እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገውን የመንፈሳዊ ስጦታዎች ትክክለኛ ገጽታ ለማግኘት ስንሞክር፣ በእግዚአብሔር የሚሰጡት ስጦታዎች አያሌ መለኮታዊ ዓላማ እንዳላቸው እንገነዘባለን፤ ይኸውም--የቤተ ክርስቲያንን ኅብረት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገርና ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ (ኤፌ. 4:12-16)፣ በመለኮት የተሰጠው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተልዕኮ ወደፊት የሚያደርገውን ግስጋሴ እንዲቀጥል ለማድረግ (ኤፌ. 4:11-12) በመጨረሻም ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ነው (1ጴጥ. 4:10-11)።

ስጦታዎች ሌላውን እንድናገለግል (1ጴጥ. 4:10)፣ መንፈሳዊ ትርፍ እንዲገኝና በቤተ ክርስቲያን መነቃቃት ለማምጣት እንጂ በግል እንድንደሰትባቸው ፈጽሞ አልተሰጡንም። በቤተ ክርስቲያን መበረታታትና መነቃቃት እንዲያመጡ የተሰጡ የእግዚአብሐር ስጦታዎች በተሳሳተ መንገድ ጥቅም ላይ እየዋሉ የጥቂቶች ዝና ሲገንባቸው መታየቱ በእጅጉ ያሳዝናል። የእንዲህ ያለው ነገር መከሰት ግለሰቦች ከመጠን ያለፈ ግላዊ ዝና እንዲያካብቱ በር በመክፈት በተቃራኒው በቤተ ክርስቲያን መከፋፈልን የሚያበረታታና መለያየትን የሚያመጣ ይሆናል።

ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ስናስብ ብዙውን ጊዜ ጉዳዩን በቀጥታ የምናያይዘው ከምንቀበለው ችሎታና መክሊት ጋር ነው። መክሊት ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጠው ራሱን የቻለ ሥራን ወይም አገልግሎትን ተንተርሶ መሆኑን ልብ ይሏል (1ጴጥ. 4:10)። ስለዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ኃያል በሆነ መንገድ፤ በተለያየ መጠን በእግዚአብሔር ይሰጣሉ ማለት እንችላን። ስጦታዎቹ--ቤተ ክርስቲያንን ለሚያሳድገው የተለየ ዓይነት አገልግሎት ግለሰቡን ገጣሚ ያደርጉታል። ወደዚያ ግብ ለመድረስ ልዩ ልዩ ስጦታዎች ሊኖሩ ይገባል።

**የስጦታዎች ተቀዳሚ ዓላማ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ማጠናከር የሆነበት ምክንያት ምን ይመስሎታል? አማኞች ከተለያዩ ስጦታዎቻቸው ጋር እንዴት ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ማነጣጠር ይችላሉ? በቤተ ክርስቲያን ያሉ የተለያዩ ስጦታዎች የመለያያ ምንጮች ከመሆን ይልቅ በረከት እንዲሆኑ ምን መደረግ ይኖርበታል?**

*ረቡዕ የካቲት 15* *Feb 22*

## ስጦታ--ያኔ እና ዛሬ

**1ቆሮ. 14:1 ካነበቡ በኋላ ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር ያስተያዩ:--1 ቆሮ. 12:7-11፣ 2731፣ ሮሜ 12:3-8፣ ኤፌ. 4:11-12። እነዚያ ስጦታዎች በሙሉ የተሰጡት ለአዲስ ኪዳን አማኞች ብቻ ነበር? ስጦታዎቹ ዛሬም መገኘት የሚችሉ የሆኑት ለምንድን ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱት መንፈሳዊ ስጦታዎች በየሱስና በሐዋርያቱ ዘመን ብቻ እንደተገደቡ አድርገው የሚያስቡ አንዳንድ ክርስቲያኖች--ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ህልፈት በኋላ መንፈሳዊ ስጦታዎቹም በቤተ ክርስቲያን መታየታቸው አክትሞለታል ሲሉ ይሞግታሉ። ለዚህ ሙግታቸው እንደ ድጋፍ ለመጠቀም የሚሞክሩት ሐዋርያው ጳውሎስ "ነገር ግን ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው ይሻራል" በማለት በ1ቆሮ. 14:1 ያሰፈረውን ሃሳብ በመንተራስ ነው። በእርግጥ ስጦታዎች የሚያከትሙበት ጊዜ አለ። ስጦታዎች የሚያከትሙት ፍጹም የሆነው ሲገለጥ ሲሆን ይኸውም በድንግዝግዝ መስታወት ውስጥ መመልከታችንን አቁመን የሱስን በዳግም ምጽአቱ ፊት ለፊት ስንገናኘው ነው። መንፈሳዊ ስጦታዎች ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ (1ቆሮ. 12:28) እንደሚሰጡ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ጳውሎስ "መንፈሳዊ ስጦታዎችን በብርቱ ፈልጉ" (1ቆሮ. 14:1) ሲል አማኞችን ያስጠነቅቃል። መንፈሳዊ ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን አካል ደኅንነት በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው። እግዚአብሔር የተናገረበት ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ እስከ ሌለ ድረስ ቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን ተልዕኮ እስክታጠናቅቅና እርሱ ዳግም እስኪገለጥ--ቃሉ ባለበት ጽናት እንዲቀጥል ፍላጎቱ እንደሆነ አድርገን መቀበል ይኖርብናል።

የእግዚአብሔር ሥራ ወደ ፍጻሜ የሚመጣው ከመጀመሪያው እጅግ በበረታ ኃይልና ብርታት ነው። ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ለዳግም ምጽአቱ እንድታዘጋጅ እስከ ተጠራች ድረስ የቤተ ክርስቲያን አባላትን የተሰጣቸውን ተልዕኮ ከግብ የሚያደርሱበትን እርዳታ ሳይሰጥ እግዚአብሔር እንዲሁ አይተዋቸውም። ነገር ግን እነዚህ ስጦታዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሊተኩም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተርታ ሊሰለፉ ፈጽሞ አይችሉም። በዚህ ፋንታ አማኞችን በማስታጠቅ፣ የክርስቶስን አካል በመገንባትና ዓለምን በቅርቡ ለሚገለጠው የሱስ በማዘጋጀት--መጽሐፍ ቅዱሳዊው ተስፋ የመፈጸሙ ማሳያዎች ናቸው።

**“ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደ ሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክንደርስ ነው” (ኤፌ. 4:11-13)። ዛሬ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚያስፈልጉ ስለመሆኑ ጥቅሱ ምን ይነግረናል?**

*ሐሙስ የካቲት 16* *Feb 23*

## *መንፈስ ቅዱስና መናፍስትን የመለየት ስጦታ*

**እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--1ቆሮ. 12:10፣ 14:29፣ 1ዮሐ. 4:1-3። *መናፍስትን የመለየት ስጦታ ያስፈለገው ለምንድን ነው?***

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መንፈሳዊ ስጦታዎች ቢኖሩም ነገር ግን ሁሉንም መንፈስ እንዳናምን--ይልቁንም ከአምላካዊው ቃል ጋር ያላቸውን መጣጣም፣ ተደጋጋፊነትና የሱስን እንደ ጌታ መቀበላቸውን መፈተን እንዳለብን ያስጠነቅቀናል። “መናፍስትን መለየት” (1ቆሮ. 12:10) በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር እንደ መጣ የሚያስመስል ሁሉ በእርግጠኝነት ከእርሱ ላይሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያንን በተሳሳተ አቅጣጫ ለመምራት የሚመኙ፣ እውነተኛዎቹን የመንፈስ ስጦታዎች አስመስለው የሚተገበሩ፣ የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩ፣ የሐሰት ትንቢት የሚናገሩ፣ የሐሰት ራእዮች ያሏቸው፣ አስመሳይ ልሳን የሚናገሩ፣ አስማታዊ የፈውስ ኃይላት፣ አሳች ምልክቶችና ድንቃድንቆች ወዘተ እነዚህ ሁሉ በዲያብሎስና በአጋንንት ኃይላት ሊተገበሩ እንደሚችሉ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል።

ዛሬም ቢሆን የመንፈስ ስጦታዎችን ተገቢነት የሚቀበሉ አንዳንዶች እንደ ልዩ ምልክቶችና ድንቃድንቆች ያሉትን አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች አግባብ የሌላቸውና ወጣ ያሉ የሚል ልዩ አጽንኦት ሲሰጧቸው ይታያል። ጳውሎስ መናፍስትን የመለየትን ማስጠንቀቂያ ስለ ልሳን ከመጥቀሱ አስቀድሞ ይኸውም “ታምራትን የማድረግ” ከሚለውና “ትንቢትን የመናገር” በሚል ካስቀመጠው በመቀጠል እንዳሰፈረው እንመለከታለን (1ቆሮ. 2:10)።

የቤተ ክርስቲያንን እውነትና አንድነት የተጠበቀ ለማድረግና አባላቷ የሐሰት ነቢያቶችን ከመከተል እንዲሁም ከሐሰተኛ ምልክቶችና ታምራቶች የተጠበቁ ለማድረግ እግዚአብሔር መናፍስትን የመለየት ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ሰጥቷታል። በቃሉ መጎልመስ፣ በሳል የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት መኖር፣ ለእግዚአብሔር ቃል በእምነትና በተግባር ታማኝ መሆን--እነዚህ አግባብ ያለውን ግምገማም ሆነ ምዘና ለማድረግ ያስችሉናል። በእርግጥ መናፍስትን ለመለየት ወይም ለመመርመር የእግዚአብሔር ቃል የማንኛውም መሰረት ሊሆን የግድ ነው። ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመፈተሽና በማመሳከር ብቻ እየሰማን ወይም እያየን ያለነው ነገር በእርግጥ ከጌታ መሆኑንና አለመሆኑን ማወቅ

እንችላለን፡፡ “የተለያዩ የማታለያ ዘዴዎችን በመጠቀም እውነተኛ የሚመስሉ ታምራቶችንና አስደናቂ ትዕይንቶችን የሚፈጽመው ሰው እምነት ሲፈተን ሰይጣን ከበስተ ኋላ መኖሩን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል… ጌታን በፍጹም ልባችን፣ አእምሮአችንና ነፍሳችን የምንፈልግባቸው ቀናት በከንቱ አይለፉብን፤ እነዚህ የከበሩ ዕድሎችም አያምልጡን፡፡ እውነትን እንዳለ በመውደድ ልንቀበለው ካልቻልን በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት በሰይጣን የሚደረጉ ታምራቶችን ከሚያዩና ከሚያምኑ አንዱ ልንሆን እንችላለን፡፡ በሐሰት አባት የሚፈበረኩ አያሌ ማሳሳቻዎች፣ እንግዳ ክስተቶችና አስደናቂ ታምራቶች ገቢራዊ ይሆናሉ… በክፉ መናፍስት ቁጥጥር ስር የሆኑ ሰዎች ታምራቶችን ያደርጋሉ፡፡”–Ellen G. White, Selected Messages, vol. 2, pp. 52, 53.

*አርብ የካቲት 17* *Feb 24*

## ተጨማሪ ሃሳብ:-

Read Ellen G. White, The Great Controversy, pp. 511-517, 593-602.

አንዳንዶች “በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የተስተዋሉት እንደ ፈውስ ዓይነት ታምራቶችን ዛሬ የማናየው ለምንድን ነው?” ብለው ይጠይቃሉ፡፡ በአንደኛ ደረጃ፡--ስለ ታምራቶች የተነገሩ ታሪኮችን በእርግጥ ሰምተናል፡፡ ደግሞም ታምራቱ ተደርጎባቸው በነበሩ ስፍራዎች አንዳንዶች ላዩት ነገር ተቀዳሚ ምስክሮች ነበሩ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፡--መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ታምራቶች ሁሌም ገቢራዊ ይሆኑ የነበሩ ክስተቶች መሆናቸውን ከግምት ማስገባት እንችላለን፡፡ ነገር ግን ያንን ስሜት ያገኘነው የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ለመመስረት አንገብጋቢ የነበሩት ክስተቶች በአብዛኛው ታምራቶችን ያካተቱ በመሆናቸውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ይህንኑ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት በመጻፋቸው ነው፡፡ በዚያን ዘመን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ከተማሩ በኋላ ምላሻቸውን ለመንፈስ ቅዱስ መሳየታቸው ያኔ የነበሩ ሁናቴዎች ባብዛኛው ከዛሬው ጋር ተመሳሳይነት እንደ ነበራቸው መገመት እንድንችል ይረዳናል፡፡

“የክርስቶስን አሠራር አስመልክቶ በመጀመሪያ ቃሉን ይሰብክና ከዚያ ለበሽተኛው ታምራዊ ፈውስ ያመጣ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰይጣን ኃይሉን ተጠቅሞ ታምራቶችን ስለሚያደርግ እኛ ዛሬ ይህን አሠራር መከተል እንደማንችል ተነግሮኛል፡፡ ከመለኮት እንደ ተላኩ የሚያስመስሉ የሐሰት የፈውስ ታምራቶች ስለሚገለጡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ዛሬ ታምራትን መሰረት ያደረገ አገልግሎት መስጠት አይችሉም፡፡ በዚህ የተነሳ ሕዝቡ አካላዊውን ፈውስ ከቃሉ አስተምህሮ ጋር አቆራኝቶ ሥራውን ወደፊት የሚያስኬድበትን መንገድ ጌታ ወስኖ ሰጥቶአል፡፡ የሕክምና ተቋማት ሊቋቋሙና ተቋማቱ ወንጌልን ከሕክምና ጋር አጣምረው አገልግሎት ከሚሰጡ እውነተኛ ባለሙያዎች ጋር ትስስር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ወገኖችን የሚታደግ በጎ አርአያነት ወደ ሕክምና ተቋማቱ የሚመጡ ሕሙማን ላይ ይሰፍናል፡፡”–Ellen G. White, Selected Messages, book 2, p. 54.

## የመወያያ ጥያቄዎች

- በመንፈስ ፍሬና በመንፈስ ስጦታዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
- ስጦታዎቹ በአፍቃሪውና ሁሉን አዋቂ በሆነው አምላክ መሰጠታቸውን ማስተዋላችን በቤተ ክርስቲያናችን ያሉትን የተለያዩ ስጦታዎች እንድናደንቅ እንዴት ሊረዱን ይችላሉ?
- ታምራዊ ፈውሶችና አስደናቂ ነገሮች በራሳቸው እውነተኛውን ነገር ለመለየት መጠበቂያችን መሆን የማይችሉት ለምንድን ነው? ከእነርሱ በተጓዳኝ የሚያስፈልገን ምንድን ነው?
- “እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ በሰጣችሁ እምነት መጠን ራሳችሁን በአግባቡ መዝኑ እንጂ፤ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን እመክራለሁ።” (ሮሜ. 12:3)። በጥቅሱ የቀረበልን አንገብጋቢ ተግሳጽ ምንድን ነው? ስለ ራሳችን ምን ያህል “ከፍ” አድርገን ማሰብ ይኖርብናል?